***AMHARIC***

**Advanced Learning**
*Mailing address: M.S. 32-936 – P.O. Box 34165   Seattle, WA  98124-1165*
*Web address*: http://www.seattleschools.org/area/advlearning/index.xml  *Phone:  206-252-0130*

# የመረጃ ጥቅል ፓኬት

**ልጄ የላቀ ትምህርት እንዲማር/እንድትማር እንዴት መምረጥ እችላለሁ ?** ወላጆች፣ አስተማሪዎች/ሰራተኞችና የኮሚኒቲ ኣባላት ተማሪዎች እንዲፈተኑ መምረጥ ይችላሉ። ነገር ግን ፈተናውን እንዲወስዱ በወላጆች/ሞግዚት የተፈረመ ፎርም ያስፈልጋል። አስተማሪዎችና የኮሚኒቲ ኣባላት ለመምረጥ ለሚፈልጓቸውን ተማሪዎች ወላጆች/ሞግዚት፡ የወላጅ/ሞግዚት ፎርሙን መስጠት አለባቸው። እንዲሁም የአስተማሪ/ሰራተኞች አስተያየት መስጫ ፎርም ያስፈልጋል። ሁለቱ ፎርሞች ጥቅምት(ኦክቶበር) 8, 2009* መመለስ አለባቸው። *(ለኪንደርጋርተን ተማሪዎች ብቻ ፡ የአስተማሪዎች/ሰራተኞች የአስተያየት መስጫ ፎርም ኖቬምበር 12, 2009 መሰጠት አለበት።)

**የመምረጫ ፎርም የት ማግኘት እችላለሁ ?** የመምረጫ ማቴሪያሎች በአንደኛና በመለስተኛ ትምህርት ቤት ጽህፈት ቤቶች፣ በባይሊንጓል ቤተሰብ ማእከልና በጆን ስታንፈርድ ማእከል በሚገኘው የመመዝገቢያ ጣቢያዎች ይገኛል። እንዲሁም ከዚህ ቀጥሎ ባለው ዌብ ሳይት ማግኘት ይቻላል። www.seattleschools.org/area/advlearning/index.xml.

**የመምረጫ ማቴሪያሎችን የምመልሰው የት ነው ?** የተሞላው የወላጆች/ሞግዚት የፈቃድ መስጫ ለትምህርት ቤታችሁ ጸሃፊ ይመልሱት። ወይም በቀጥታ ከላይ በተጠቀሰው የልቀት ትምህርት ጽህፈት ቤት ይላኩት። የወላጅ/ሞግዚት የፈቃድ ፎርም ለአስተማሪዎች አትስጡ። አስተማሪዎች/ሰራተኞች የአስተያየት መስጫ ፎርሙን ለትምህርት ቤት ጸሃፊ መስጠት ወይም በትምህርት ቤት የውስጥ መላላኪያ ፖስታ ወይም የዩናይትድ ስቴትስ ፖስታ ኣድርገው መላክ ይችላሉ። እንዲሁም የመምረጫ ፎርሞች ወደ ጆን ስታንፈርድ የትምህርት ማእከል በመሄድ መስጠት ይቻላል። አድራሻው ደግሞ 2445 third Ave. S ነው። ፋክስ የተደረገና በኢሜል የሚላክ መጠየቂያ ፎርም አንቀበልም። የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ቤተሰቦች ማቴሪያሉን ወደ የልቀት ትምህርት ጽህፈት ቤት ከ $ 90 ዶላር ጋር መላክ ይኖርባቸዋል። ወይም ወደ ጆን ስታንፈርድ ማእከል በግንባር በመሄድ መስጠት ይችላሉ።

**ከሲያትት ትምህርት ቤቶች ክልል ውጭ ኗሪ ከሆንኩኝ ልጄ እንዲፈተን/እንድትፈተን መምረጥ እችላለሁን ?** አይቻልም። ተማሪዎች ለመፈተን በሲያትል ትምህርት ቤቶች ክልል ውስጥ መቀመጥ ይኖርባቸዋል። ወይም በሲያትል ትምህርት ቤቶች ትምህርት ቤት የሚማሩ መሆን አለባቸው።

**ልጄ ፈተና የሚያደርግበት ቀን መቼ እንደሆነ ይገለጽልኛል ወይ ?** አዎ። ፈተና የሚደረግበት ቀንን የሚገልጽ ደብዳቤ ይላክላችኋል። በኖቬምበር(ህዳር) ኣጋማሽ አካባቢ የሚፈተኑበትን ቀን የሚገልጽ ደብዳቤ ካልደረሳችሁ ከልቀት ትምህርት ጽህፈት ቤት ጋር ይገናኙ። የአስተሳሰብ ችሎታ ፈተና(ኮግኒቲቭ) በኦክቶበር መጨረሻ እስከ ዲሰምበር አጋማሽ ድረስ ይደረጋል። የስራ ውጤት(ኣቺቭመንት) ፈተና ደግሞ በጃንዋሪ(ጥር) ኣጋማሽ 2010 ይጠናቀቃል። አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ፈተናዎችን ቅዳሜ ይሰጣሉ።

**የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሚፈተኑት መቼ ነው?** በአሁኑ ወቅት በሲያትል ትምህርት ቤቶች የማይማሩ ተማሪዎች የሚፈተኑበት ቀን ቅዳሜ ነው። ፈተናው በተለያዩ የሲያትል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይደረጋል። ፈተና የሚሰጥባቸውን ቦታዎችና ቀኖች መረጃ የያዘ ደብዳቤ ከኦክቶበር 8 በኋላ ባሉት ቀናት በፖስታ ወይም በኢሜል ይላክላችኋል። አንዳንድ ተማሪዎች ለመፈተን ሁለት ቅዳሜዎች ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ይህም በሚወስዱት የአስተሳሰብ ችሎታ ውጤት መሰረት ይሆናል።

**ወላጆች ልጆቻቸው በሚፈተኑበት ወቅት መታዘብ ይችላሉን ?** አይችሉም። ፈተና የሚወስዱ ተማሪዎቻችንን ሊረብሽ ይችላል። ተማሪዎች የሚታዘቡ ሰዎች በአካባቢያቸው በማይኖሩበት ወቅት ይበልጥ ሊሰሩ ይችላሉ።

**የልጄን የፈተና ውጤት መቼ አውቃለሁ ?** የመጨረሻው የብቁነት ውጤትና ነጥቦችን በጃንዋሪ 29 , 2010 አካባቢ ይላካል። የፈተና ውጤትና የብቁነት ውጤት የሚገለጸው በደብዳቤ ብቻ ነው። ከዛ በፊት በቴሌፎን ሆነ በፋክስ አይገለጽም።

**የመምረጫ ፎርሞች የሚመለሱበት ቀን ኦክቶበር 8, 2009 ነው።**

*Mailing address: M.S. 32-936 – P.O. Box 34165 Seattle, WA 98124-1165*
*Web address*: http://www.seattleschools.org/area/advlearning/index.xml *Phone: 206-252-0130*

**የሚሰጡት ፈተናዎች ምን አይነት ናቸው። ?** ሁሉም ተማሪዎች የአስተሳሰብ ችሎታ መለኪያ ፈተናን ይወስዳሉ። በተጨማሪ የንባብና የሂሳብ የስራ ውጤት(አቺቭመንት) ፈተናም ሊያስፈልግ ይችል ይሆናል። የዋስል የስራ ፍሬ-ውጤቶች(በስፕሪንግ 2009 ከተደረገ)፣ ወይም ማፕ( ሜዠር ኦፍ አካዳሚክ ፕሮግሬስ፡ በትምህርት ቤታችን በፎል ወራት 2009 የሚሰጥ አዲስ ፈተና ልንጠቀም እንችላለን። በቅርቡ የተደረገ የስራ ፍሬ-ውጤቶች በፋይል የሌላቸው ተማሪዎች ውድኮክ ጆንሰን አችቭመንት ቴስት(ለኪንደርጋርተን እስከ 1ኛ ክፍል)፣ አዮዋ ቴስት ኦስ ቤዚክ ኢንግሊሽ( ከ 2ኛ እስከ 7ኛ ክፍል) ወይም የማፕ ፈተና ይሰጣቸዋል። ለስፔክትረም ያንግ ስኮላርስ ፕሮግራም(1ኛ-2ኛ ክፍል) ብቁ ለመሆን የአቺቭመንት ፈተና አያስፈልጋቸውም። ለተጨማሪ ዝርዝር መግለጫዎች እባክዎን ዌብሳይታችንን ተመልከቱ። www.seattleschools.org/area/advlearning/eligtestcriteria.htm

**የንባብና የሂሳብ የስራ ስኬታማነት(አቺቭመንት) ፈተናዎችን በግምት ውስጥ እንዲገቡ ማቅረብ ይቻላልን ?**
በአሁኑ ወቅት በሲያትል ትምህርት ቤቶች የማይማሩ ተማሪዎች ሆነው በንባብና በሂሳብ የስራ ስኬታማነት ፈተናዎችን በትምህርት ቤት ክልል ሆነው ከማርች 1,2009 የወሰዱ፡ ያገኙት ነጥብ እንዲታይላቸው ማቅረብ ይችላሉ። የፈተናው ነጥቦች በልቀት መማሪያ ጽሕፈት ቤት ከዲሰምበር 16, 2009 በፊት መቅረብ አለበት። በብሄራዊ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው ነጥቦች(አይቲቢኤስ፡ ኢአርቢ) ወይም የዋስል ነጥቦች ብቻ ናቸው። የሚቀርቡት የፈተና ነጥቦች በተማሪው መዝገብ ይቀመጣል። በአስተሳሰብ ችሎታ ፈተና ምትክ ግን አይቆጠሩም። ።

**አንድ ተማሪ ብቁ አይደለም ከተባለ፡ ውሳኔውን ይግባይ ለማለት የሚችልበት አሰራር አለን ?** **አዎ።**
ይግባይን የሚመለከት ዝርዝር መረጃ ብቁነትን በሚገለጸው ደብዳቤ ላይ ይገለጻል። እንዲሁም በልቀት ትምህርት ዌብሳይት ላይ ይገኛል። የግል መምዘኛዎች ተቀባይነት ያላቸው በይግባይ ሂደት ወቅት ብቻ ነው።

**ተማሪዎች ብቁነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን በየአመቱ መፈተን አለባቸውን ?** በፕሮግራም ተሳታፊ የሆኑ ተማሪዎች እንደገና መፈተን አያስፈልጋቸውም። በአክሰሌሬትድ ፕሮግሬስ ፕሮግራም(ኤፒፒ)፣ በስፔክትረም ፕሮግራም ወይም በአድቫንስድ ለርኒንግ ኦፖርቹኒቲ(ኤኤልኦ) ትምህርት ቤት የሚማሩና የላቀ ትምህርት የስኬታማነት ፈተና ሪፖርት ያገኙ ተማሪዎች ብቁነታቸውን ይዘው ለመቆየት እንደገና መፈተን አያስፈልጋቸውም። ይህ ከ 5ኛ እስከ 6ኛ ክፍል የሚሸጋገሩ ተማሪዎችንም ይመለከታል። **በ 2009-10 ለፕሮግራሙ በቂ ሆነው የተገኙ ተማሪዎች፡ ተመዝግበው ካልተማሩ ለ 2010-11 እንደገና መፈተን ይኖርባቸዋል።** በፕሮግራሙ ለመግባት ያመለከቱ ተማሪዎች ሆነው ነገር ግን በተጠባባቂ ስም ዝርዝር ያሉ ተማሪዎች ይራዘምላቸዋል። ነገር ግን ለቀጣዩ አመት የምዝገባ ወቅት ከመዘጋቱ በፊት መመዝገብ አለባቸው ወይም ዳግማይ ፈተና ይወስዳሉ።

**የብቁነት ፈተና ለ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች አለን ?** የለም። በኢንተርናሽናል ባካሎሬት ፕሮግራም(በሲልዝና ኢንግርሃም ት/ቤቶች የሚሰጥ፡ ) ለመግባት የብቁነት ፈተና አያስፈልግም። ወይ ደግሞ የአድቫንስድ ፕሌስመንት ትምህርትቶች(በዘጠኝ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች) የሚሰጠውን ለመማር ፈተና አያስፈልግም።

***ልጄ በግል ትምህርት ቤት ነው የተማረው። የተማሪውን መታወቂያ ቁጥር ምን መጠቀም አለብኝ?**
ልጅዎ ከዚህ በፊት በሲያትል ት/ቤቶች ለመመዝገብ ወይም ለመፈተን አመልክተው ከሆነ፡ ልጅዎ የሲያትል ትምህርት ቤቶች መታወቂያ ቁጥር ይኖረዋል/ራታል። በግል ት/ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች ወላጆች፡ ስለ የሲያትል ት/ቤቶች መታወቂያ ቁጥር እውቀት የሌላቸው ወይም መታወቂያ ቁጥር የሌላቸው መሞላት ያለበትን ቦታ እንዲሁ ክፍት አድርገው መተው ይችላሉ። የሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥራችሁን አትጻፉበት።

***በመምረጫው ፎርም ላይ ዘር የተጠየቀበት ምክንያት ለምንድን ነው ?** በሲያትል ትምህርት ቤቶች መታወቂያ ቁጥር በሚሰጥበት ወቅት ዘር አስፈላጊ ነው። እንዲሁም መታወቂያ ገና ለሌላቸውም አስፈላጊ ነው። ልጅዎ በአሁኑ ወቅት በሲያትል ትምህርት ቤቶች ያልተመዘገበ/ች ከሆነና እንዲሁም የሲያትል ት/ቤቶች መታወቂያ ቁጥር የሌለው ከሆነ/ች ከዚህ ቀጥለው ካሉት አንዱን ይምረጡ፤ AI: አሜሪካን ኢንድያን ; AN አላስካን ኔቲቭ ; BL ብላክ ; CH ቻይኒዝ ; ኢስት ኢንድያን ; FI ፍሊፒኖ ; GY ጂፕሲ ; HA ሂስፓኒክ ኤዥያን ወይ ፓስፊክ አይላንደር ; HB ሂስፓኒክ ብላክ ; HI ሂስፖኒክ ኢንድያን ; HWሂስፓኒክ ዋይት ; JN Jጃፓኒዝ; KO ኮሪያን NA ኔቲቭ አሜሪካን ወይ ካልእ አላስካን ኔቲቭ ; OA ሌላ ኤዥያን ወይ ፓስፊክ አይላንደር; SA ሳሞአን ; SO ሳውዝኢስት ኤዥያን ; VI ቬትናሚዝ ; WH ዋይት .

**የመምረጫ ፎርሞች የሚሰጡበት ቀን ኦክቶበር 8, 2009 ነው**

SEATTLE PUBLIC SCHOOLS

*AMHARIC*

**Advanced Learning**

*Mailing address: M.S. 32-936 – P.O. Box 34165 Seattle, WA 98124-1165*

*Web address*: http://www.seattleschools.org/area/advlearning/index.xml *Phone: 206-252-0130*

**የልቀት ትምህርት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ምንድን ናቸው ?** የልቀት ትምህርት ፕሮግራሞች ውስብስብና የተፋጠነ ትምህርትን ልዩ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች የሚሰጥ ነው። የልቀት ትምህርት ተማሪዎች ከሁሉ አይነት ባህሎች፣ ቋንቋና ማህበረ-ኢኮኖሚ የተውጣጡና የተለያየ ችሎታና የመገብየት ገጽታ ያላቸው ናቸው። እነዚህ ተማሪዎች ለምርምር፣ ለመቀያየር፣ ወሳኝና የፈጠራ አስተሳሰቦችን የሚያበረታታና የሚኮሰኩስ የተለያዩ አይነት ፕሮግራሞች የሚያስፈልጋቸው ናቸው። የልቀት ትምህርት ፕሮግራሞችንና ብቁነትን ለማወቅ መፈተንን እንዲሁም የኮሌጅ ቦርድ አስተዳደርና/የልቀት ምደባ ፈተናዎችን የሚያቀነባብረው የልቀት ትምህርት ጽህፈት ቤት ነው።

| ፕሮግራም | የክፍል ደረጃዎች | የብቃት ፈተና | ካሪኩለም(ሰርዓተ ትምህርቲ) |
|---|---|---|---|
| የልቀት ትምህርት እድሎች (ALO) | 1-8 | አያስፈልግም | በንባብና በሂሳብ ጥልቀት ያለውና የተፋጠነ ስርአተ ትምህርትን ይሰጣል |
| ስፔክትረም ያንግ ስኮላርስ | 1-2 | አዎ | በንባብና በሂሳብ የተቀላጠፈ ስርአተ ትምህርት(በተለይ ካሉበት የክፍል ደረጃ በአንድ አመት ከፍ ያለ) |
| ስፔክትረም | 3-8 | አዎ | በንባብ(እንግሊዝኛ ስነጥበብ) ሂሳብ የተቀላጠፈ ስርአተ ትምህርት(በተለይ ካሉበት የክፍል ደረጃ በአንድ አመት ከፍ ያለ) |
| አክሰሌሬትድ ፕሮግረስ ፕሮግራም (APP) | 1-8 | አዎ | በንባብና (እንግሊዝኛ ስነ ጥበብ) ሂሳብ ተማሪዎች በሚያስፈልጋቸው መሰረት የተቀላጠፈ ስርአተ ትምህርት(በተለይ ካሉበት የክፍል ደረጃ በሁለት አመት ከፍ ያለ) |
| ኢንተርናሽናል ባካላውሬት | 9-12* | አያስፈልግም | ጥልቀት ያለው (ሪጎረስ) የሁለተኛ ደረጃ ስርአተ ትምህርት፡ አለም አቀፋዊ ይዘት ባላቸው ፕሮግራሞች የተዘጋጀና ለኮሌጅ ነጥብን ሊያስገኝ የሚችል |
| አድቫንስድ ፕሌስመንት | 9-12* | አያስፈልግም | በኮሌጅ ቦርድ የሚሰጥና በኮሌጅ ነጥብ ሊያስገኝ የሚችል ጥልቀት ያለው የሁለተኛ ደረጃ ስርአተ ትምህርት |

*በሁለተኛ ደረጃ የሚሰጡ ፕሮግራሞችን ለመማር የብቁነት ፈተና አያስፈልግም። ለ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች ደግሞ ፈተና የለም።

**ልጄ ለፕሮግራሞቹ እንዲፈተን/ትፈተን ለማድረግ ልጄን መምረጥ እችላለሁን ?** በምትመርጡበት ወቅት በግምት ውስጥ የምታስገቧቸው ዝርዝር ባህርዮች ቀጥለው ተጠቅሰዋል፤

**የመናገር ችሎታና**
- ✓ ለእድሜው/ዋ ተመጣጣኝ የሆነ ቃላት አለው/አላት
- ✓ ያለማቋረጥ ያወራል/ታወራለች፡ ጥያቄንም ይጠይቃል/ትጠይቃለች

**አስተሳሰብ ናይ የአስተሳሰብ ችሎታ**
- ✓ በአይነ ህሊና ያያል/ታያለች፣ ብዙ ሃሳቦች አሉት/አላት
- ✓ ለጥያቄዎች በርካታ ግሩም የሆኑ መልሶችን መስጠት ይችላል/ትችላለች

**የመማር ባህርዮች**
- ✓ መረጃዎችን ቶሎ ብሎ ይረዳል/ትረዳለች፣ የሚማረውን ያስታውሳል /ታስታውሳለች
- ✓ ይበልጥ አስቸጋሪ በሆኑ ነገሮች ላይ መስራት ይፈልጋል/ትፈልጋለች፣ የተለመዱ ስራዎችን ላይጨርስ/ላትጨርስ ይችላል/ትችላለች፡ ምክንያቱም ይበልጥ አሳሳቢ ነው ብሎ በሚያስባቸው ፕሮጀክቶች ላይ ግዜውን ማጥፋት ይፈልጋል/ትፈልጋለች።

**በራስ ተነሳሽነት**
- ✓ በአንዳንድ ርእሶች/ፕሮጀክቶች ላይ በጣም ፍላጐት ያሳያል/ታሳያለች እንዲሁም ሁሉጊዜ ጊዜውን በነሱ ላይ ያጠፋል/ታጠፋለች
- ✓ ስራን ለመጨረስ ብዙ መመሪያዎች አያስፈልገውም/ጋትም። እራሱ/ሷ ማወቅ ይፈልጋል/ትፈልጋለች

**ማሕበራዊና ስሜታዊ እድገት**
- ✓ ስለ ሌሎች ስሜት ይጠነቀቃል፡ እንዲሁም ፍትህን በሚመለከት ግድ ይለዋል/ይላታል
- ✓ ሁሉም ትክክል እንዲሆን የሚፈልግ ይሆናል/ ስህተት ሲገኝ ይርበተበታል
- ✓ ከእድሜው በላይ ከሆኑ ሰዎች ጋር ጊዜ ማሳለፍ ይመርጣል

**ምንባብ**
- ✓ ጠንካራ አንባቢ ነው፣ ካለበት የክፍል ደረጃ በላይ ያነባል/ታነባለች ወይም በቀዳሚዎቹ እድሜው ያነባል/ታነባለች

**የሂሳብ ችሎታ**
- ✓ ስለ ሂሳብ በጣም ፍላጐትን ያሳያል፣ ካለበት የክፍል ደረጃ በላይ ያለ ሂሳብን ይሰራል/ትሰራለች ወይም በቀዳሚዎቹ እድሜው/ዋ ስለ ሂሳብ ፍላጐትን ያሳያል/ታሳያለች

**ለተጨማሪ መረጃ እባክዎን ዌብሳይታችንን ተመልከቱ**

http://www.seattleschools.org/area/advlearning/index.xml

***AMHARIC***

**Advanced Learning**
*Mailing address: M.S. 32-936 – P.O. Box 34165 Seattle, WA 98124-1165*
*Web address*: http://www.seattleschools.org/area/advlearning/index.xml *Phone: 206-252-0130*

# የወላጅ/ሞግዚት የፈቃድ መጠየቂያ ፎርም

**(ሁሉንም አይነት ፈተናዎች ከመፈተን በፊት የተፈረመ የመምረጫ ፎርም ያስፈልጋል። )**

| | |
|---|---|
| የተማሪው አያት ስም/ ላስት ኔም   መጠሪያ ስም   የአባት ስም/ሚድል ኔም | የሲያትል ት/ቤቶች መታወቂያ ቁጥር # (አስፈላጊ)* |
| የወላጅ/ሞግዚት ስም( እባክዎን ይጻፉት) | የክፍል ደረጃ (09-10) |
| የቤት አድራሻ   ዚፕኮድ | አሁን የሚማሩበት ት/ቤት (09-10) |
| ቴሌፎን ቁጥር | የልደት ቀን |
| የኢሜል አድራሻ | ጾታ |
| ልጅዎ በግል የትምህርት ፕላን(አይኢፒ) ወይም 504 ፕላን ላይ እንደተጠቀሰው ልዩ በፈተና ወቅት ማሻሻያ የሚያስፍፈልገው ከሆነ እዚህ ላይ ምልክት ያድርጉ። የ 504 ፕላን ኮፒ ከፈተናው በፊት ከላይ በተገለጸው አድራሻ መሰረት ይላኩት። ☐ | በቤት ውስጥ ተዘውትሮ የሚነገር ቋንቋ |
| ልጅዎ ከዚህ በፊት በሲያትል ትምህርት ቤት የልቀት ትምህርት ፕሮግራም ተመርጦ፣ ተፈትኖ ያውቃልን / አዎ___________/አላውቅም________________መልስዎ አዎ ከሆነ በየትኛው አመተ ምህረት / | ዘር * |

***የሲያትል ት/ቤቶች ተማሪዎች ወላጅ/ሞግዚት፤***

**ልጄ በልቀት ትምህርት ፕሮግራም እንዲፈተን/እንድትፈተን እፈቅዳለሁ። ለሁሉም ተማሪዎች የአስተሳሰብ ችሎታ(ኮግኒቲቭ) ይፈተናሉ። እንዲሁም የትምህርት መገብየት ፈተና(አቺቭመንት) ይሰጣል።ለይቶ ለማወቅ፣ የፕሮግራም አማራጮና ሰለ ይግባይ አባባል መግለጫዎች ተሰጥቶኛል።** (WAC 392-170-047).

*ፊርማዎ* ________________________________________________________**እለት** ______________________

***የግል ትምህርት ቤት ወላጅ/ሞግዚት፡***

**ልጄ በልቀት ትምህርት ፕሮግራም እንዲፈተን/እንድትፈተን እፈቅዳለሁ። ለሁሉም ተማሪዎች የአስተሳሰብ ችሎታ(ኮግኒቲቭ) ይፈተናሉ። እንዲሁም የትምህርት መገብየት ፈተና(አቺቭመንት) ይሰጣል።ለይቶ ለማወቅ፣ የፕሮግራም አማራጮና ሰለ ይግባይ አባባል መግለጫዎች ተሰጥቶኛል።** (WAC 392-170-047).

*ፊርማዎ* __________________________________________________________________*ቀን* __________________________

**(በአሁኑ ወቅት በሲያትል ትምህርት ቤቶች የማይማሩ ተማሪዎች ለስራ ማስኬጃ ፡ የማይመለስ $ 90 ዶላር አያያዘው መላክ አለባቸው)**

*ፊርማ አስፈላጊ ነው* WAC 392-170-04

*በሁለተኛው ገጽ ያለውን የመረጃ ፓኬት እባክዎን ይመለከቱ።

***ለሁሉም የክፍል ደረጃዎች የወላጅ/ሞግዚት የፈቃድ መስጫ ፎርም የሚመለስበት ቀን ኦክቶበር 8, 2009 ነው።
የፈቃድ መስጫውን ፎርም በጆን ስታንፈርድ የትምህርት ማእከል መጥተው ወይም ወደ ልቀት ትምህርት ጽህፈት ቤት በፖስታ መላክ ትችላላችሁ። በአሁኑ ወቅት በሲያትል ት/ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች ፎርሙን በሚማሩበት ት/ቤት ጽህፈት ቤት መስጠት ይችላሉ።***